የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party(EPRP)

ታህሣሥ 11 ቀን 2004 ዓ.ም

# ወያኔ ሀገር መሸጡን ገፍቶበታል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሀገርን ለባዕድ መሸጥ ከጀመረ ውሎ አድሯል:: ቻይናውም፤ ህንዱም፤ አረቡም ሌላውም ሁሉ የሀገራችንን መሬት እየተቀራመቱ ናቸው:: ወያኔ የቋራን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለግሶ እነሆ እስከዛሬ በከሀዲነት እየተወገዘ ነው::

ይህ ክህደትና ሀገርን መጉዳቱ ሳይበቃ ወያኔ በቅርቡ ከሱዳን ጋር ባደረገው ስብሰባ የተፈረመው ስምምነት የሱዳን ዜጎች ሁሉ - ዘላኖቹን ጨምሮ - በነፃ ወደ ኢትዮጵያ መሬት የመዝለቅ መብትን ሰጥቷቸዋል:: ይህንን በባሕር ዳር ስብሰባ በትግራይ ክልልና በሱዳኖች መሀል የደራ ንግድ እንዲካሄድ ስምምነትን አፅደቋል:: በአልፋሻጋና በምዕራብ ትግራይ መሀል ነፃ ንግድ መባሉም ተዘግቧል:: የወያኔ ጦር ስደተኞችን በማሳደድ በአል ጋዲ በኩል ወደ ሱዳን ገብቶ እንዲንቀሳቀስም ሱዳን ፈቃድ ለግሷል:: የሱዳን ዘላኖች፣ ከብት አርቢዎች፣ ...ወዘተ ወደ ኢትዮጵያ በነፃ ገብተው ይንቀሳቀሱ በሚል የተሰጠው ፍቃድ አንድም ሀገርን የሚያጠፋ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ነገ መሬቱም የእኛ ነው ብለው የሚሰየሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል:: ወያኔ ሀገርን መሸጥ ዋና ስምሪቱ ሆኖ ይገኛል:: በገዳሪፍና አዋሳኝ የኢትዮጵያ ክፍሎች መሀል ግንኙነቱ በሁሉም መስክ ይስፋፋ የተባለውም ለኢትዮጵያ የሚበጅ አለመሆኑ ግልፅ ነው:: በባህር ዳሩ ስብሰባ የተካፈለው የሱዳን ተጠሪ ያህያ ሀምዳዬን ሃሳበሲዶ እንደገለፀው በሱዳንና ወያኔ መሀል የፀጥታና ደህንነት ስምምነቱ ዋና ሲሆን ይህም ስምምነት ውጤታማ እንደሚሆን ይጠበቃል ተብሏል:: የሱዳን አገዛዝ ኢትዮጵያዊ ስደተኞችን ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱ በተደጋጋሚ የተዘገበ መሆኑም ይታወሳል:: ወያኔ የሀገራችንን መሬትና ዜጎችንም ለሱዳን አሳልፎ እየሰጠ እያለ ሀገር ወዳድ ነን የሚሉ ሁሉ ዝምታን መምረጣቸው በጣም አነጋጋሪ ሆኗል::

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን እያወገዘ በቅርቡ ወያኔና ሱዳን የተፈራረሙትን ስምምነትንም በጥብቅ ያወግዛል:: ለሱዳን ዜጎች - ዘላኖች፣ አራሾች፣ ...ወዘተ በነፃ ግቡ ብሎ ፈቃድ መስጠቱ ሀገርን ለዝርፊያ አጋላጭ ነውናም ኢሕአፓ የሚቃወመውና የሚፃረረው ስምምነት ነው::

በጋራና በቆራጥነት ሀገራችንን እናስከበር!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com